# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር

# ስፖርት ምክር ቤት

# የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር

# መመሪያ ቁጥር

# 12/2018ዓ.ም

2018 ዓ/ም

አዲስ አበባ

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት**

**የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ**

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት ባለው ኃላፊነት መሰረት ይህንን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ፡-**

1.1. ይህ መመሪያ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የስፖርት ምክር ቤት የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 12/2018 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

2.1. **"ቢሮ"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርቱን በበላይነት እንዲመራ በአዋጅ ስልጣን የተሰጠው ተቋም ማለት፡፡

2.2. **"ስፖርት ምክር ቤት"** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት በመመሪያ ቁጥር 007/2014 የተቋቋመ ም/ቤት ነው፡፡

2.3. **የስፖርት ምክር ቤት ገቢ፡-** ማለት ስፖርት ምክር ቤት ከመንግስት ድጋፍ ከዕርዳታ፣ ከስጦታ፣ከስፖርት ማዕከላት ከውድድር፣ ከሜዳ ገቢ፣ ከስፖንሰርሺፕ፣ ከማስታወቂያና ከመሳሰሉት በራሱ የሚሰበሰበው ገንዘብና ንብረት ማለት ነው፣

2.4. **የመንግስት ድጋፍ ፡-** ማለት ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ዕድሣትና ጥገና፣ ለትምህርት፣ ለስልጠና፣ ለውድድር፣ ለንቅናቄና ተሳትፎና ለሌሎች የስፖርት ተግባራት የሚሰጥ የድጋፍ ገንዘብ ነው፡፡

2.5. **የስፖርት ማህበራት፡-** ማለት በአዲስ አበባ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እውቅና አግኝቶ በፌዴሬሽን፣ በአደራጅ ኮሚቴ፣ በስፖርት ኮሚቴ፣ በአሶሴሽን ደረጃ የተቋቋመና ስፖርትን በከተማው አስተዳደር ለመምራትና ለማስፋፋት ኃላፊነት የተሰጠው አካል ነው፡፡

2.6. **የሥራ ክፍሎች ፡-** ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስፖርቱን እንቅስቃሴ ለመምራት የተቋቋሙ የስፖርት ትምህርትና ስልጠና ማዕከላት፣ የተለያዩ ዳይሬክቶሬቶች፣ ቡድኖችና ደጋፊ የስራ ሂደቶችን ያጠቃልላል፣

2.7. **ሰው፡-** ማለት በተፈጥሮ ሰው የሆነ ሰብአዊ መብቱ የተከበረለት ማለት ነው፡፡

## 3. የባንክ ሂሳብ

3.1 የስፖርት ምክር ቤት በስሙ የተከፈተ የባንክ ሂሳብ ይኖረዋል፣

3.2 የስፖርት ምክር ቤቱ ለከተማው አስተዳደር ስፖርት እንቅስቃሴ የሚሰበስበው ገንዘብ በምክር ቤቱ ስም በተከፈተው የባንክ ሂሳብ ብቻ ገቢ ይደረጋል፣

## 4. ሂሳብ ስለማንቀሳቀስ

4.1 የስፖርት ምክር ቤት ሂሳብ በምክር ቤት የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ም/ሰብሳቢና በክፍያና ሂሳብ ዳይሬክቶሬት /ቡድን መሪ/ በጣምራ ፊርማ ይንቀሳቀሳል፡፡

4.2 በስፖርት ምክር ቤት ለስፖርት ማህበራት የተፈቀደ በጀት በስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይም ም/ፕሬዝዳንት፣ ፅ/ቤት ኃላፊ፣ ፋይናንስ ባለሙያ ወይም ዓቃቢ ነዋይ ተጠይቆ ከተረጋገጠ በኋላ ለስራ አስፈጻመ ቀርቦ ሲፈቀድ ወጪ ይሆናል፣

4.3 ለስፖርት ምክር ቤት አስተዳደራዊ ስራዎች የተፈቀደ በጀት በወጣቶችና ስፖርት ቢሮ የስራ ክፍሎች ተጠይቆ ለስፖርት ምክር ቤት ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይም ም/ሰብሳቢ ቀርቦ ሲፈቀድ ወጪ ይሆናል፣

4.4 ማንም ሰው በስፖርት ምክር ቤት የወጪ ማዘዣ ላይ ራሱ ጠያቂ፣ ራሱ አረጋጋጭ፣ አፅዳቂ ፈቃጅና ወሳጅ ሊሆን አይችልም፤

4.5. የክ/ከተማና የወረዳ ስፖርት ም/ቤት ሂሳብ በስፖርት ምክር ቤቱ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ፣ ም/ሰብሳቢና የክፍለ ከተማ ሆነ በወረዳ ምክርቤቱ ያለበተ ፑል ፋይናስ ቡድን መሪ ጣምራ ፊርማ ይንቀሳቀሳል፣

## 5. የስፖርት ምክር ቤት የገቢ አሰባሰብ

5.1 የስፖርት ምክር ቤት ገቢ በስሙ በሚዘጋጀው የገቢ ማሰባሰቢያ ደረሰኝ ብቻ ይሰበሰባል፣

5.2 ማንኛውም የስፖርት ምክር ቤት ገንዘብ ወጪ ከመሆኑ በፊት በምክር ቤቱ የባንክ ሂሳብ ገቢ መደረግ አለበት

5.3 የስፖርት ምክር ቤት ገንዘብ አሰባሰብ በዚህ የፋይናንስ መመሪያ ብቻ ይሆናል፤

## 6. የፋይናንስ አጠቃቀም

6.1 ስፖርት ማህበራቱ የገቢ አሰባሰብና የወጪ ስርዓት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስፖርት ምክር ቤት በወጣው በዚህ የፋይናንስ መመሪያ መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል፤

**6.2** ከመንግስት የድጋፍ ገንዘብ ላይ የሚወጣው ወጪ በስፖርት ም/ቤቱ ወይም በማህበሩ ስም በሚከፈተው አካውንት ገንዘቡ ተቀምጦ ለስራ ይንቀሳቀሳል፣

**6.3** ለስፖርት ማህበራት ከመንግስት የሚሰጠው ድጋፍ ከስፖርት ምክር ቤት አካውንት በጥቅሉ በሰነድ ለስፖርት ማህበሩ ወጪ ሆኖ ይሰጣል፣ በሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኞችም ሂሳቡ ይወራረዳል፣

**6.4** የስፖርት ማህበሩ ወጪዎች የሚፈፀሙት በስፖርት ምክር ቤት በሚታተሙ የወጪ ደረሰኞች ብቻ ይሆናል፣

**6.5** ለስፖርት ማህበራት ጥቃቅን ወጪዎች በማህበሩ ገንዘብ ያዥ እጅ ብር 10,000 /አስር ሺህ/ ወጪ ሆኖ ይቀመጣል፣

**6.6** የስፖርት ማህበሩ ወጪ ከብር 10,000 /አስር ሺህ/ በላይ ከሆነ በቼክ ይፈፀማል፣

**6.7** የስፖርት ማህበሩ ወጪዎች ከህጋዊ ማስረጃዎች ጋር ተዘጋጅተው በማህበሩ ፅ/ቤት ሀላፊ ለስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይቀርባሉ፣

**6.8** የስፖርት ማህበሩ ዓቃቤ ነዋይ የሚቀርቡለትን የወጪ ማስረጃዎች ተመልክቶና ህጋዊነታቸውን አረጋግጦ በፋይናንስ መመሪያው መሰረት መፈፀማቸውን መርምሮ ወጪዎች እንዲፀድቁ ያቀርባል፣

**6.9.** ከፔቲካሽ በስተቀር ሌሎች ወጪዎች በተመለከተ፡-

6.9.1. የስፖርት ማህበሩ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ቃለ ጉባኤና ውሳኔ ከገንዘብ መጠየቂያው ሰነድ ጋር ተያይዞ በስፖርት ማህበሩ ፅ/ቤት ኃላፊ በኩል መቅረብ አለበት፣

6.9.2. ገንዘብ ወጪ የሚደረገው የገንዘብ መጠየቂያው ሰነድ በስፖርት ማህበሩ ተዘጋጅቶና በስፖርት ማህበሩ ፕሬዝዳንት፣ በፅ/ቤት ኃላፊና በፋይናንስ ባለሙያ ፊርማ ሲፀድቅ ብቻ ነው።

**6.10.** ለትምህርትና ስልጠና፣ ለውድድር፣ ለንቅናቄና ተሳትፎና ለሌሎች የስፖርት ተግባራት የሚወጡ የስፖርት ማህበሩ ማናቸውም ወጪዎች በስፖርት ምክር ቤት የክፍያ ተመን መሰረት ብቻ ይፈፀማሉ፣

**6.11.** የስፖርት ማህበራት የራሳቸውን የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ይህንን መመሪያ በተከተለ መልኩ ማውጣት ይችላሉ፣

## 7. የፋይናንስ ሰነድ አያያዝ

- የገቢና የወጪ መረጃዎች የሂሳብ መዛግብት ለምርመራ በሚያመች መንገድ ተለይተው በጥንቃቄ በፅህፈት ቤቱ መቀመጥ አለባቸው፣

## 8. የገንዘብ አሰባሰብ

8.1 ለስፖርት ምክር ቤቱም ሆነ ስፖርት ማህበራት እንቅስቃሴ በተለያየ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ በስፖርት ምክር ቤቱ ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማንም ሰው ገንዘቡን ሊሰበስብ አይችልም፣

## 9. የስፖርት ምክር ቤት ዓመታዊ በጀት

9.1. የስፖርት ምክር ቤት ዓመታዊ በጀት ለአንድ በጀት ዓመት በምክር ቤቱ የፀደቀ በጀት ነው፣

9.2. የስፖርት ምክር ቤት የበጀት ዓመት ከመስከረም 1 ቀን እስከ ጳጉሜ 5 ወይም 6 ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፣

9.3. የስፖርት ምክር ቤት ዓመታዊ በጀቶች የገቢና የወጪ በጀት ተብለው ይታወቃሉ፣

**9.4.** በስፖርት ምክር ቤት ለተለያዩ ስራዎች ከፀደቀው በጀት ተራፊው ገንዘብ ወደ ስፖርት ምክር ቤቱ ሂሳብ ተመላሽ ይሆናል፤